የሰይጣንን ተንኮል ወደ ጉትጎታ የመለሰው አላህ ምስጋና ይገባው።" አሉ።

ኢብኑ ዐባስ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ ብለዋል፦ አንድ ሰው ወደ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው
ላይ ይስፈን በመምጣት እንዲህ አለ፦ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንዳችን እሱን ከመናገር ይልቅ አመድ መሆን የሚያስደስተውን ነገር
በነፍሱ ውስጥ ይሰማዋል።" እርሳቸውም፦ "አላሁ አክበር አላሁ አክበር የሰይጣንን ተንኮል ወደ ጉትጎታ የመለሰው አላህ ምስጋና
ይገባው።" አሉ።
[ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድና ነሳኢ በኩብራ ዘግበውታል።]

አንድ ሰው ወደ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በመምጣት እንዲህ አለ፦ የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንዳችን በነፍሱ ውስጥ የሚመላለስ ነገርን በውስጡ ይሰማዋል። ነገር ግን እሱን ከመናገር ይልቅ አመድ መሆን እስኪመኝ ድረስ እሱን መናገር ይከብደዋል። መልክተኛውም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሁለት ጊዜ ተክቢር በማሰማት የሰይጣንን ተንኮል ወደ ጉትጎታ ብቻ በመመለሱ አላህን አመሰገኑ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65012